Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 35
ADDIS ABABA 7th July, 2006

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፱/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ከናይጄሪያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፬፻፴፯

**CONTENTS**

**Proclamation No. 499/2006**

The Government of Federal Democratic Republic of Nigeria Bilateral Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation…. Page 3437

### አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፱/፲፱፻፺፰

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በናይጄሪያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የአየር አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በናይጄሪያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. በጁላይ ፭ ቀን ፪ሺ፭ በአቡጃ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸምን በተመለከተ ሕገ መንግሥታዊ ሥነ-ሥርዓቶች መፈጸማቸውን ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እርስ በርሳቸው ካስታወቁበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 499/2006.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE BILATRAL AIR TRANSPORT SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF NIGERIA

**WHEREAS,** a Bilateral Air Transport Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Federal Democratic Republic of Nigeria was signed in Abuja on 5th day of July 2005;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force on the date of the last notification of notes from either contracting parties confirming its ratification in accordance with its laws and regulation;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement on its meeting held on the 20th day of June, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Ministry of justice



## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከናይጄሪያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፱/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በናይጄሪያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፭ ቀን ፪ሺ፭ አቡጃ ላይ የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "The Government of Federal Democratic Republic of Nigeria Bilateral Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation No.499/2006."

## 2. Ratification of the Agreement

The Bilateral Air Transport Services Agreement signed in Abuja on the 5th day of July 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Federal Democratic Republic of Nigeria, is hereby ratified.

## 3. Power of the Minister of Transport and communication

The Minister of Transport and communication is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**